# የሻዕቢያ አገዛዝ ዋጋው ሳይንር .....

Wednesday, 25 March 2015 10:59

•

በሳምሶን ደሣለኝ



የኢትዮጵያ አየር ኃይል ተዋጊ ጀቶች ሁለት የተመረጡ ቦታዎችን ወደ ኤርትራ ዘልቀው መደብደባቸው በተለያዩ ሚዲያዎች ተዘግቧል። ድብደባ ከተፈጸመባቸው ቦታዎች አንዱ ከአስመራ **150** ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኘው ባይሻ የወርቅ ማዕድን ማውጫ ቦታ ሲሆን ይህን የወርቅ ማዕድን ማውጫ የካናዳው ኔቨሰን ኩባንያ ከአስመራ አገዛዝ ጋር በመሆን በሽርክና ወርቅ የማውጣቱን ስራዎች ያከናውናል። ሌላው በማይ እዳግ ትኩል በተባለ አካባቢ የሚገኘውን የወታደራዊ መሳሪያዎች ቁሳቁስ ማከማቻ ቦታ የአየር ድብደባ ከተፈጸመባቸው አንዱ ነው።

ከኢትዮጵያ አየር ሃይል ጥቃት በኋላ ተቀማጭነቱ ካናዳ የሆነው የኔቨሰን ኩባንያ በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ በወርቅ ማዕድን ማውጫው ላይ ድብደባ መፈጸሙን አምኖ የደረሰው አደጋ ግን አነስተኛ መሆኑን አስታውቋል። የተፈጠረው አደጋ ወደ ወርቅ ማዕድን ማውጫው በሚገባው የውሃ መስመር ላይ አነስተኛ ጉዳት ቢያጋጥምም አፋጣኝ ጥገና በማድረግ ወደ ስራ መግባታቸውን አስታውቋል። የወርቅ ማዕድን ማውጫው ስልሳ ከመቶ የሚሆነው በካናዳው ኔቨሰን ባለቤትነት የተያዘ ሲሆን የኤርትራ አገዛዝ አርባ በመቶ የሚሆነውን የአክስዮን ድርሻ ይዟል።

የሰንደቅ ጋዜጣ ምንጮች በበኩላቸው የኢትዮጵያ አየር ኃይል የአስመራን ግዛት አቋርጧ መደብደቡን ማረጋገጫ ሰጥተዋል። ሆኖም የኢትዮጵያ መንግስት ይህን የአየር ጥቃት ለመፈጸም ያስገደደውን ምክንያቶች ከማስቀመጥ ተቆጥቧል። በርግጥ የኢሳያስ አገዛዝን በአየር ለማጥቃት ብቻ ሳይሆን ጭራሹኑ ከኢትዮጵያ እና ከአስመራ ሕዝቦች ጫንቃ ላይ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለማስወገድ ከአንድ ሺ በላይ ምክንያቶች ማስቀመጥ ይቻላል። የዚህ ፁሁፍ አቅራቢ በጣም የቅርብ ምክንያቶችን አንስቶ ለምን ይህ ድብደባ እንደተፈጸመ ለማሳየት ይሞክራል። ማስተላለፍ የተሞከረውስ መልክቶች ምንድን ናቸው**?**

ድብደባውን ለመፈጸም በመሰረታዊነት ከሚነሱት ሁለት ምክንያቶች የሚጠቀሱት አንዱ የኢትዮጵያ አየር ኃይል ንብረት የሆነው የጦር ሔሊኮፕተር ሀገራቸውን በከዱ የአየር ኃይል መኮንኖች አስመራ ማረፉ የሚታወስ ሲሆን፣ እስካሁን ተመላሽ አልሆነም። ሁለተኛው፣ የኢሳያስ አገዛዝ በአዲስ መልክ ኢትዮጵያን ለማተራመስ እየሰሩ መሆናቸው ነው።

## የጦር ሔሊኮፕተር

ከኢትዮጵያ አየር ኃይል የከዱ መኮንኖች አንድ ተዋጊ የጦር ሔሊኮፕተር ይዘው ወደ አስመራ መግባታቸው ይታወሳል። ይህን የጦር ሔሊኮፕተር ለማስመለስ የተለያዩ ጥረቶች ቢደረጉም ማስመለስ አልተቻለም። በተለይ ኢሳያስ ይህን አጋጣሚ በመጠቀም ወደ ዓለም ዓቀፍ ሚዲያ አውታሮች ብቅ በማለት የወደቀውን የአገዛዙን ሞራል ለመመለስ ተጠቅመውበታል። ሁለቱ ሀገሮች በጦርነት ከበባዊ ሁኔታዎች ውስጥ የሚገኙ በመሆናቸው የጦር ሔሊኮፕተሩ የመመለስ እድሉ አነስተኛ ነው የሚባለው። ስለዚህም የኢሳያስን አገዛዝ ጫና ውስጥ በመክተት የጦር ሔሊኮፕተሩን ለማስመለስ

የተወሰደ እርምጃ ሊሆን ይችላል ተብሏል።

## የኢሳያስ አገዛዝ ቃለ ምልልስ ውስጥ

ኢሳያስ አፈወርቂ ለኢሳት ቴሌቪዥን ጣቢያ የሰጡት ቃለ ምልልስ በጥንቃቄ ላዳመጠው ኢትዮጵያዊ፣ የሻዕቢያ አገዛዝ አሁንም በኢትዮጵያ ሕዝብና ጥቅም ላይ ስትራቴጂክ ጠላት መሆኑን ለመገንዘብ የሮኬት ሳይንስ አይፈልግም። ከሁሉም በላይ ኢሳያስ ከስህተት ለመማር ያልተዘጋጁና በቀጣይም ስህተታቸውን ለማረም ተነሳሽነት የሌላቸው መሆኑን መረዳት ይቻላል።

ኢሳያስ ወይም የሻዕቢያ አገዛዝ አሁንም በኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩ ሕዝቦች መንግስታቸውን ለማወቅና ለመተንተን አቅም እንደሌላቸው አድርገው ያስባሉ። የሻዕቢያ አገዛዝ አመራሮች አሁንም ድረስ መንቃት ያልቻሉበት የበሽታ አይነት፣ ለራሳቸው በሰጡት ግምት የሚሰቃዩበት በሽታ ሲሆን፤ ከተጠናወታቸው ግማሽ ምዕተ ዓመት ሊሞላቸው ጥቂት ዓመታት ነው የቀራቸው። በአንድ ሀገር ውስጥ ያለውን የፖለቲካ ሁኔታ መለወጥ የሚችሉት ለፖለቲካው ባለቤት የሆኑ ሕዝቦች ብቻ መሆናቸው ግልፅ ነው።

ኢሳያስ በቃለ በምልልሳቸው ያነሱት ፍሬ ነገሮች ለተዘነጋ ኢትዮጵያዊ ሊያቀብሉት የሚፈልጉት የፖለቲካ አጀንዳዎች ናቸው። በሀገራቸው ሕገ መንግስትና ሕገ መንግስታዊ ስርዓት ያልዘረጉት ኢሳያስ፣ የኢትዮጵያ ሕገ መንግስት በጠባብ አዕምሮ የተቀረጸ ነው ሲሉ በአደባባይ ተናግረዋል። ሕገ መንግስቱ ምንም ይሁን ምንም መቼም ሕገ መንግስት ከሌላት ሀገር እና በሕገ መንግስት ለማስተዳደር ፍላጎት ከሌለው መሪ ትችት መስማት አስገራሚ ነው። ምክንያቱም በሕገመንግስት መመራትን በመሰረታዊ አስተሳሰብነት የማይቀበል የሀገር መሪ ስለማንኛውም ሕገ መንግስት አስተያየት ቢሰጥ ሰሚ አያገኝም። የሞራል ብቃትም የለውም።

ኢሳያስ በኢትዮጵያ ሕገ መንግስት አንቀጽ **39** ላይ የሰጡት አስተያየት ከሁሉም በላይ አንድ ማሰብ ለሚችል ኢትዮጵያዊ ያላቸውን ንቀት የሚያሳይ ነው። ይህም ሲባል እሳቸውና ግብር አበሮቻቸው ኤርትራን በጦርነት በኃይል አስገንጥለው ሲያበቁ ኢትዮጵያን የምታክል ትልቅ ሀገር በሕገ መንግስቷ እስከ መገንጠል የሚል አንቀጽ መቀመጡን “እኛ (ሻዕቢያዎች) ቀደም ብለንም አልተቀበልነውም። በዚህ ጉዳይ ላይም ምንም ያደረግነው ነገር የለም። የሚጸጽተን ነገር የለም።” ብለዋል። በዚህ ደረጃ ኢሳያስ ሲናገሩ የኤርትራን መገንጠል ምን ያህሉ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደሚደግፈው ዳታ የሰበሰቡ ይመስሉ። እሳቸውና ጓዶቻቸው ዛሬ ለገነጠሏት ኤርትራ ያህል ዓመት እንደፈጀባቸው መገመትስ እንዴት ተሳናቸው?

ኢሳያስ የኢትዮጵያ ፌደራል ስርዓት ሕዝቦችን አፋጥቶ ለመግዛት ያለመ ስትራቴጂ እንጂ የፌዴራል ስርዓት የሚባል የለም። ክልሎቹም በአዲስ መልክ የተዋቀሩት ሕዝቡን ከፋፍሎ ለመግዛት የታለመ መሆኑን አስቀምጠዋል። ኢትዮጵያን የምታክል ሀገር ወደ ክልል ደረጃ መከፋፈል ተገቢ አይደለም ሲሉ ተቃውሞቸውንም አሰምተዋል። ኢሳያስ ይህን የተቃውሞ ምላሻቸውን ሲያሰሙ በኢትዮጵያ ውስጥ በምርጫ ቦርድ ተመዝግበው የሚወዳደሩ ተቃዋሚ ፓርቲ እንጂ የሌላ ሀገር መሪም አይመስሉም።

ኢሳያስ በጣም አስገራሚ ምላሻቸው በሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ የሰነዘሩት ወቀሳ ነው። ሕወሓት በተደጋጋሚ ሲያነሱ አንድ አናሳ ቡድን እያሉ ሲሆን፤ ኢሳያስ “ይህ አናሳ ቡድን ሀገር እቆጣጠራለሁ ብሎ ሲያስብ በአስተሳሰቡ መጠን የሚያስከትላቸው መዘዞች አሉ” ሲሉ ከሰዋል። በዋናነት የሚያነሱት በኢትዮጵያና በኤርትራ ሕዝቦች መካከል ለተፈጠረው የተበላሸ ግንኙነት ሕወሓትን ተጠያቂ በማድረግ ነው። ለዚህ የኢሳያስ ክስ ሻዕቢያ ማን እንደሆነ? በኢትዮጵያ ስትራቴጂክ ጥቅም ላይ የቆመ ደንቃራ አገዛዝ መሆኑን፣ የአቶ ገብሩ አስራት “ሉአላዊነት እና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ” የሚለውን መጸሐፍ አንባቢያን እንዲያነቡት ይመከራል። ሌላ ምን ይባላል።

በአጠቃላይ ሲታይ የሻዕቢያ አገዛዝ ምን እንደሚያስብ? ምን ማድረግ እንደሚፈልግ? በኢሳት ቴሌቪዥን ላይ ኢሳያስ የሰጠው ቃለ ምልልስ ያመላክታል። ከዚህም በላይ ርቆ ሄዶ፣ ሻዕቢያ ጦር ላነሱ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ሃይሎች ሁሉንም አይነት ድጋፍ እየሰጠ ይገኛል። ግልፅ የሽብር ጥቃቶች በኢትዮጵያ ላይ ያደራጃል፣ ያሰማራል። ሻዕቢያ የሚሰጠው ድጋፍ መነሻውም ምን እንደሆነ በኢሳያስ ቃለ ምልልስ ላይም ማስተዋል ተችሏል። ስለዚህም ሻዕቢያን ከዚህ በላይ ርቆ ሄዶ የሚያስከፍለው ዋጋ ከመናሩ በፊት፣ አሁን ባለው ዓለም ዓቀፍ፣ አህጉር አቀፍ እና በሀገር ውስጥ የመገለል ፖለቲካዊ ቁመና ላይ እያለ አገዛዙ ላይ የሚደረገውን የዲፕሎማሲ ጫና ማሳደግና ያልተገቡ ተግባራቱን ቀጣይነት ባለው መልኩ ማጋለጥ ይገባል።